ጁን 2019

# የመኖሪያ ቤቶች ጽ/ቤት

## አገልግሎቶች እና መርሃ ግብሮች

421 King Street, Suite 215
Alexandria, VA 22314

703-746-4990
www.alexandriava.gov/housing

ስለ ከተማ የመኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣ ለ **eNews** ይመዝገቡ! እባክዎን **www.alexandriava.gov** የሚለውን ድረ-ገጽ በመጎብኘት ‘ያነጋግሩን’ የሚለውን ይጫኑ እና ለ eNews ይመዝገቡ። ከዚያም “አቅምን ያገናዘቡ የመኖሪያ ቤት እድሎች” የሚለውን ይምረጡ።

## ለቤት ገዢ የመረጃ ግብዓቶች

www.alexandriava.gov/74590

### አቅምን ያገናዘቡ የቤት ባለቤትነት ክፍሎች

አቅምን ያገናዘቡ መልሶ ለመሸጥ ገደብ ያላቸው ክፍሎችን ያስተዋውቃል።

ብቁ የሚሆኑት፥ እስከ 100% AMI ድረስ ገቢ የሚያገኙ ዝቅተኛ- እና መካከለኛ-ገቢ ያላቸው የመጀመሪያ ጊዜ የመኖሪያ ቤት ገዢዎች *(የስለገቢ ገደቦች በገጽ 2 ላይ ይመልከቱ)*

የሚያነጋግሩት፥ **Vicente Espinoza**
vicente.espinoza@alexandriava.gov
**Brandi Collins**
brandi.collins@alexandriava.gov

### ቤት ገዢዎችን ማማከር

ለመጀመሪያ ጊዜ ቤት ገዢዎች በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ በነጻ የቤት ገዢዎች ማማከር እና ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ ክፍለ ጊዜዎች የ VHDA የስልጠና ስርዓተ ትምህርትን የሚከተሉ ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤት ገዢዎች ለ VHDA ከገበያ በታች ዝቅ ያሉ የወለድ ተመኖች እና የከተማው የመኖሪያ ቤት ግዢ ብድሮች ለማግኘት ተደራሽነት ይሰጣሉ።

ብቁ የሚሆኑት፥ የመጀመሪያ ጊዜ የመኖሪያ ቤት ገዢዎች

የሚያነጋግሩት፥ **Vicente Espinoza**
vicente.espinoza@alexandriava.gov

በተጨማሪም በ www.vhda.com ላይ VHD A ን ይጎብኙ

### የቤት ባለቤትነት ድጋፍ ብድሮች

በከተማው የሚረዱ ንብረቶች ለመግዛት ከወለድ ነጻ በሆነ መልኩ ለቅድመ ክፍያዎች ሳይከፈሉ የቆዩ ክፍያዎች ብድር፣ እና/ወይም የቀረ ክፍያን ለማጠናቀቅ ወጪዎች ብድሮች ይሰጣል። በተጨማሪም፣ ከተማው በ VHDA የማህበረሰብ የቤት ባለቤትነት ማስዋብ ፕሮግራም በኩል በ VHDA ፋይናንስ የሞርጌጅ ወለድን ለመቀነስ የሚያስችሉ የገንዘብ ፈንድ ተደራሽነት ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ እስከ 100% AMI ድረስ ገቢ የሚያገኙ ዝቅተኛ- እና መካከለኛ-ገቢ ያላቸው የመጀመሪያ ጊዜ የመኖሪያ ቤት ገዢዎች *(የስለገቢ ገደቦችን በገጽ 2 ላይ ይመልከቱ)*

የሚያነጋግሩት፥ **Vicente Espinoza**
vicente.espinoza@alexandriava.gov

## የመኖሪያ ቤት እቅድ

ስለ ከተማው *መኖሪያ ቤት ለሁሉም ፖሊሲዎች*፣ አቅምን ያገናዘበ የመኖሪያ ቤት ግቦች፣ እና የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች የበለጠ ለማወቅ እባክዎ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፥

**www.alexandriava.gov/HousingPlan**

### የመኖሪያ ቤት ችግር አጋጥሞዎታል?

እባክዎትን በስልክ ቁጥር **703-746-5700** ለማህበረሰብ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ (DCHS) ይደውሉ።

ቀጠሮ ሳያስይዙ ለመጎብኘት በ 2525 Mount Vernon Avenue, Alexandria, VA 22301 አድራሻ የሚገኘውን የ DCHS ቢሮን ይጎብኙ።

## ለተከራይ የመረጃ ግብዓቶች

www.alexandriava.gov/74591

### አቅምን ያገናዘቡ የሚከራዩ ክፍሎች

አቅምን ስላገናዘቡ የሚከራዩ ግብዓቶች መረጃ ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ ዝቅተኛ- እና መካከለኛ-ገቢ ያላቸው ተከራዮች

የሚያነጋግሩት፥ **Irma Garcia**
irma.garcia@alexandriava.gov
**Melodie Seau**
melodie.seau@alexandriava.gov

በከተማው ውስጥ ያሉ አፓርትመንት ህንጻዎችን ለማነጻጸር የ 2019 የአፓርትመንት የዳሰሳ ጥናታችንን በ www.alexandriava.gov/housing (የተከራይ የመረጃ ግብዓቶች) ላይ ይመልከቱ።

በቨርጂኒያ ውስጥ **ተደራሽነት ያላቸው** ኪራዮችን ጨምሮ ለሌሎች አማራጮች፣ www.virginiahousingsearch.com የሚለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

### የአከራይ-ተከራይ እና የመኖሪያ ቤት የማማከር አገልግሎቶች

በአከራዮች እና ተከራዮች መካከል የሚፈጠሩ ከመኖሪያ ቤቶች ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያግዝ ሲሆን፣ የመኖሪያ ቤቶችን በተመለከተም የምክር አገልግሎትን ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ ሁሉም የከተማው ተከራዮች

የሚያነጋግሩት፥ **Gwen Lassiter**
gwen.lassiter@alexandriava.gov
**Goodman Okpara**
goodman.okpara@alexandriava.gov

### የህዝብ መኖሪያ ቤቶችና የመኖሪያ ቤቶች ምርጫ (ክፍል 8) ቫውቸሮች

የአሌክሳንድሪያ የመኖሪያ ቤት ማሻሻያ ባለስልጣን (ARHA) በከተማው ውስጥ የህዝብ መኖሪያ ቤቶችን ያሉት እና የሚያስተዳድር ሲሆን የመኖሪያ ቤት ምርጫ ቫውቸሮችንም ያስተዳድራል።

የሚያነጋግሩት፥ **Janell Diaz**, (703) 549-7115
401 Wythe Street, Alexandria, VA 22314
www.arha.us

### ቤት በሚቀየርበት ወቅት የሚደረግ እገዛ

መኖሪያ ቤትን ስለመቀየር የሚገልጹ ደንቦችን በተመለከተ ለአከራይዮች እና ተከራዮች መረጃ ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ ሁሉም የከተማው ተከራዮች

የሚያነጋግሩት፥ **Irma Garcia**
irma.garcia@alexandriava.gov

### የኪራይ ተደራሽነት ማሻሻያ ፕሮግራም

የአካል ጉዳት ላለባቸው ብቁ ተከራዮች የተደራሽነት ማሻሻያዎች ለማድረግ እስከ $50,000 ድረስ ድጋፍ ይሰጣል። እስከ $2,800 በሚደርሱ የማስተካከያዎች ለማገዝ "አነስተኛ ድጋፎችን" ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ እስከ 80% AMI ድረስ ገቢ የሚያገኙ ዝቅተኛ- እና መካከለኛ-ገቢ ያላቸው የአካል ጉዳተኛ ተከራዮች *(ስለገቢ ገደቦች በገጽ 2 ላይ ይመልከቱ)*

የሚያነጋግሩት፥ **Brandi Collins**
brandi.collins@alexandriava.gov

# እርዳታ ለማግኘት ብቁ ነኝ?

ቤተሰቦች ለአንዳንድ የከተማው የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች ብቁ ለመሆን የሚጠበቁትን የገቢ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። የገቢ ገደቦች እንደ ፕሮግራሙ አይነት እና የቤተሰብ መጠን የሚለያዩ ሲሆን፣ በአሜሪካ የመኖሪያ ቤቶች እና የከተማ ልማት መምሪያ በሚሰላ ክልላዊ አማካይ የገቢ መጠን ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የ 2019 የገቢ ወሰኖችን ለማየት፣ እባክዎትን በቀኝ በኩል ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| % የአካባቢው አማካይ ገቢ (AMI) | የ 2019 ዓመታዊ የገቢ ወሰኖች በቤተሰብ ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 1-ሰው | 2-ሰው | 3-ሰው | 4-ሰው | 5-ሰው* |
| የ AMI 30% | $25,500 | $29,150 | $32,800 | $36,400 | $39,350 |
| የ AMI 40% | $34,000 | $38,840 | $43,680 | $48,520 | $52,440 |
| የ AMI 50% | $42,500 | $48,550 | $54,600 | $60,650 | $65,550 |
| የ AMI 60% | $51,000 | $58,260 | $65,520 | $72,780 | $78,660 |
| HUD 80% | $54,350 | $62,100 | $69,850 | $77,600 | $83,850 |
| የ AMI 80% | $68,000 | $77,680 | $87,360 | $97,040 | $104,880 |
| የ AMI 100% | $85,000 | $97,100 | $109,200 | $121,300 | $131,100 |

**ምንጭ፥** HUD፣ የመኖሪያ ቤት ጽ/ቤት *የገቢ ወሰኖች 6+ ቤተሰብ ላላቸውም ቤተሰቦችም ተግባራዊ ይሆናሉ

## የቤት ባለቤት የመረጃ ግብዓቶች www.alexandriava.gov/97057

### የቤት መልሶ ግንባታ የብድር ፕሮግራም (HRLP)

የግንባታ ህግ ጥሰቶችን፣ የግንባታ ቋሚ ክፍል ችግሮች፣ ለሊድ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ የኃይል ማሻሻያዎችን፣ እና ሌሎች ጥገናዎችን ለማድረግ ከወለድ ነጻ የሆነ እና ወደፊት መክፈል ሊጀምሩ ቃል ገብተው የሚወስዱት ብድር እስከ $135,000 ዶላር (ለጋራ መኖሪያ ቤቶች እስከ $75,000 ዶላር) ድረስ ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ እስከ 80% AMI ድረስ ገቢ የሚያገኙ ዝቅተኛ- እና መካከለኛ-ገቢ ያላቸው የቤት ባለቤቶች *(የገቢ ወሰኖችን ይመልከቱ)*

የሚያነጋግሩት፥ **Arthur Thomas**
arthur.thomas@alexandriava.gov

### ማማከር እና ስልጠና

ለመጀመሪያ ጊዜ ቤት ገዥዎች በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ **በነጻ** የቅድመ-ግዢ ስልጠና ይሰጣል። በተጨማሪም፣ ከተማው ግብዓቶችን እና ጥቆማዎችን፣ እንዲሁም የገንዘብ አስተዳደርን፣ የግል በጀት አያያዝን፣ መደበኛ እና ያልተከፈሉ ክፍያዎች፣ የቤት እገዳን መከላከል፣ እና በጋራ መኖሪያዎች ውስጥ ሲኖሩ የባለቤትነት መብቶች እና ኃላፊነቶችን ጨምሮ በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ የማማከር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

ብቁ የሚሆኑት፥ ሁሉም የከተማው ነዋሪዎች

የሚያነጋግሩት፥ **Vicente Espinoza**
vicente.espinoza@alexandriava.gov

ለአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም 100% ከአገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆነ የአካል ጉዳት ላለባቸው አባት አርበኞች ስለ ከተማው **የሪል-ስቴት የታክስ እርዳታ** ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ www.alexandriava.gov/TaxRelief የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 703.746.3901 ይደውሉ (አማራጭ 6 ን ይምረጡ)።

## የመኖሪያ ቤት መድልዎ የመረጃ ግብዓቶች

### የሰብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት

የከተማው የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ተፈጻሚ የሚባል መድልዎ ካለ በመመርመር ጸረ-መድልዎ ህጎችን ተፈጻሚ ያደርጋል፣ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፥

- የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ወይም ኪራይ
- የመኖሪያ ቤት ማስታወቂያ
- ለአካል ጉዳተኝነት ማስተካከያዎች ወይም ማሻሻያዎች
- ለመኖሪያ ቤት ግዢ፣ ግንባታ፣ እድሳት ወይም ጥገና የሚሆን ብድር

የሚያነጋግሩት፥ **Jean Kelleher**, (703) 746-3140
www.alexandriava.gov/humanrights

### ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ምርመራ

በመኖሪያ ቤት ኪራይ እና የሽያጭ ገበያዎች እና የሞርጌጅ ብድር ላይ አድልዎ መኖር እና አለመኖሩን ለማጣራት ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ምርመራ ያካሂዳል።

የሚያነጋግሩት፥ **Goodman Okpara**
goodman.okpara@alexandriava.gov

### ለወኪሎች እና የንብረት አስተዳዳሪዎች ስልጠና

ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤቶች ህጎችን በተመለከተ ለሪል-ስቴት እና የንብረት አስተዳደር ኩባንያዎች የስልጠና ሴሚናሮችን ይሰጣል።

የሚያነጋግሩት፥ **Melodie Seau**
melodie.seau@alexandriava.gov

## ሌሎች የመኖሪያ ቤት የመረጃ ግብዓቶች

### የመኖሪያ ቤት አልባነትን መከላከል እና የኪራይ እፎይታ

**የማህበረሰብ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ**

- የመኖሪያ ቤት አልባነት ምዘና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት (HSAC) ድንገተኛ መጠለያ ለሚፈልጉ እንደ ዋና መግቢያ ሆኖ ያገለግላል።
- የማህበረሰብ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (OCS) ብቁ ለሆኑ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና የመኖሪያ ቤት ችግር ላጋጠማቸው ሰዎች የኪራይ እርዳታ ይሰጣል።

ማንኛውንም አይነት የ HSAC ወይም የ OCS አገልግሎቶች ለመጠየቅ፣ እባክዎትን በስልክ ቁጥር (703) 746-5700 ይደውሉ ወይም የብቁነት ማጣሪያ ለማድረግ 2525 Mount Vernon Avenue, Alexandria, VA 22301 ወደሚገኘው የ DCHS ጽ/ቤት ብቅ ይበሉ።

### ቤት ለሚለቁ እቃ ማከማቻ

**የማህበረሰብ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ** ብቁ ለሆኑ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና ከመኖሪያቸው ወዲያው ተገደው የመልቀቅ ችግር ላጋጠማቸው ሰዎች ለቤት እቃዎች ማከማቻ እና የድንገተኛ መጠለያ ሪፈራል መጠነኛ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።

(703) 746-5700

### የቤት ጥገና አገልግሎቶች

**በአንድ ላይ አሌክሳንድሪያን መገንባት (RTA)** ብቁ ለሆኑ የመኖሪያ ቤት ባለቤቶች ነፃ የቤት ጥገና፣ የደህንነት ማሻሻያዎች፣ እና የኃይል ፍጆታ ማሻሻያዎችን ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ www.rebuildingtogetheralex.org የሚለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

(703) 836-1021

### የነዳጅ እርዳታ

**የቨርጂኒያ የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ** በነዳጅ እርዳታ መርሃ ግብር በኩል ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ቤተሰቦች ይረዳል። እባክዎትን 2525 Mount Vernon Avenue, Alexandria, VA 22301 በሚገኙት የ DCHS ቢሮዎች በአካል በመቅረብ ወይም በኦንላይን www.dss.virginia.gov/benefit/ea/ ላይ ያመልክቱ።

### መጠለያዎች

**የአሌክሳንድሪያ ማህበረሰብ መጠለያ**

2355-B Mill Road, Alexandria, VA 22314
(703) 746-3660

**ካርፔንተርስ ሼልተር**

5701-D Duke Street, Alexandria, VA 22304
(703) 548-7500